የሰ/መ/ቁ. 114816

ግንቦት 26 ቀን 2008 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች ፡- ዳዊት በለጠ የጠጠር አምራች ድርጅት -ጠበቃ እሸቱ አሰፋ -ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አብዱራዛቅ ሙሳ ኡስማን -አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ ህግ ከደነገገው ውጭ አመልካች የስራ ውሌን አቋርጧል፤ ስለሆነም ለህገውጥ ስንበት በህጉ የተፈቀደው ልዩ ልዩ ክፍያዎች ይከፈለኝ በማለት የክፍያ አይነቶችን ዘርዝሮ ዳኝነት ሲጠይቅ፤ የአሁን አመልካች በበኩሉ ተጠሪ ከነሀሴ 30 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ በመደዳ ከስራ የቀረ በመሆኑ የስራ ውሉ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27/1/ለ/ ስር በተመለከተው መሰረት እንዲቋረጥ ተደርጓል፡፡ ስለዚህ ስንብቱ ህጋዊ ስለሆነ ክፍያ ልንጠየቅ አይገባም፡፡ የ25 ቀን የዓመት እረፍት እንከፍላለን በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች ምስክሮቹን ለማቅረብ በተያዘው ቀጠሮ ቀን ያላቀረበ ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 199/1/ መብቱ የታለፈ መሆኑን በመግለፅ፤ አመልካች ያቀረበው ማስረጃ ስለሌለ ስንብቱ ህገወጥ ነው በማለት ልዩ ልዩ ክፍያዎችን በማስላት በድምሩ ብር 23,000 ለተጠሪ እንዲከፍል ሲል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በስር ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ተቀባይነት ስላለገኘ በትእዛዝ ሰርዞታል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች ሰኔ 17 ቀን 2007 ዓ.ም በፃፉት የሰበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ:- ማስረጃ የማሰማት መብት የታለፈው በግልፅ የተካደ ፍሬ ነገር በማስረጃ ሳይነጥር አምነዋል ተብሎ ውሳኔ መሰጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተብሎ እንዲሻርልን ወጪና ኪሳራ እንዲተካልን የሚል አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

የአመልካች የሰበር አብቱታ ተመርምሮ በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሰረት ታህሳስ 18 ቀን 2008 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርበዋል ፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ እንደተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

የአመልካች ጥያቄ የማስረዳት መብት በማለፍ በማስረጃ ሳይረጋገጥ ውሳኔ መሰጠቱ ተገቢ አይደለም የሚል ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ ደግሞ አመልካች አዲስ ነገር በማቀረቡ ክሱ የሚከፍተው ተከሳሽ በመሆኑ በስር ፍርድ ቤት የተከሳሽ የማሰረዳት ኃለፊነቱ ነው ማለቱ የሚነቀፍ አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን የተሰጣቸው የስር ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት የአሁኑ አመልካች ምስክሮቹ እንዲያቀርብ በተያዘው ቀጠሮ አለመቅረቡን ነው፡፡

ክስን መክፈትና ሙግትን የመጀመር መብት የከሳሽ ነው፡፡ ነገር ግን ተከሳሹ ከሳሽ ያቀረበውን ክስ አምኖ ነገር ግን ሕግ ወይም ሌላ ፍሬ ነገር በመጥቀስ የቀረበብኝ ክስ ዋጋ የለውም ብሎ የሚከራከር ከሆነ ሙግቱን የሚጀምረው ተከሳሹ እንደሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 258/1/ ስር ተመልክቷል፡፡ ከሳሽ በማስረጃ አቀራረብ ረገድ ጀማሪ የሚሆነው ሁል ጊዜ እንዳልሆነ የስነ ስርዓት ህጉ በግልፅ ይደነግጋል፡፡

ወደ ያዝነው ጉዳይ ስንመለስ በተጠሪ የቀረበው ክስ የስራ ስንብቱ ህገወጥ ነው የሚል ሲሆን አመልካች ደግሞ ከስራ ያሰናበተው መሆኑን በማመን ነገር ግን በተከታታይ የስራ ቀናት በመቅረቱ ስንብቱ ህገወጥ ሊባል አይችልም የሚል ነው፡፡ እዚህ ላይ አመልካች ተጠሪን ከስራ ማሰናበቱን ከተቀበለ ፤ ለስንብቱ ምክንያት የሆነው የተጠሪ ጥፋት መሆኑን የማስረዳት ሸከሙ የስር ተከሳሽ የአሁኑ አመልካች ነው፡፡ ተጠሪ በተከታታይ የስራ ቀናት መቅረቱን ማረጋገጥ ያለበት አመልካች እንጂ ተጠሪ እንዲያስረዳ አይጠበቅም፡፡ አመልካች ምስክሮቹን እንዲያቀርብ በተያዘው ቀጠሮ ባለማቅረቡ የታለፈበት መሆኑ ከስር መዝገብ ተመልክቷል፡፡

ተጠሪ ከህግ ውጭ ከስራ ስላሰናበተኝ ተገቢውን ክፍያ ይከፈለኝ የሚል ክስ ያቀረበው አመልካች ያሰናበተው መሆኑን አምኖ የተሰናበተው በተጠሪ ጥፋት መሆኑን ገልፆ ስለተከራከረ መጀመሪያ ማስረዳት ያለበት አመልካች ነው፡፡ ነገር ግን በአመልካች ጉድለት ምክንያት ምስክሮቹን በማቅረብ ማስረዳት አልቻለም፡፡ በማስረጃ ያልተደገፈ የፍሬ ነገር ክርክር ረቺ ሊሆን አይችልም፡፡ ስለዚህ ከላይ በተዘረዘሩ ምክንያቶች አመልካች ማስረጃ ሳይሰሙ መወሰኑ አግባብ አይደለም ሲል ያቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የለውም፡፡ ሲጠቃለል የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚሁ መሰረትም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.54094 ሚያዝያ 28 ቀን 2007 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ /ፍ/ቤት በመ/ቁ. 10627 ሰኔ 4 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በፌ/መ/ደ/ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 57878 የተጀመረው አፈፃፀም ታግዶ እንዲቆይ በዚህ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከተው አካል ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ